የኢትዮጵያ ደረጃ

ኢ.ደ **6662:2021**

የመጀመሪያ ዕትም

xx-xx-2021

desa lege

Digitally signed by desalege
DN: cn=desalege, o=ESA, ou=standard development, email=desalegne46@gmail.com, c=ET
Date: 2020.10.12 11:59:36 +03'00'

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

የዳቦ ኬክ ኩኪስና ደረቅ ጣፋጭ ብስኩቶች ማምረቻና መሸጫ ተቋማት ንፅህና እና የአካባቢ ጤና አተባበቅ መስፈርት

ICS:xx .ЁЁ.

Published by Ethiopian Standards Agency

©ESA

መቅድም (foreword)

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ንፅህና እና የጤና ነክ ተቋማትአገልግሎት ቴክኒክ ኮሚቴ (ቴኮ 205) ላይ መሰረት አድርጎ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው።

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ኢደ 6662:2021፤ ይህ የ|ትዮጵያ ደረጃ በሁሉም የዳቦ፣ ኬክ፣ ኩኪስና ደረቅ ጣፋጭ ብስኩቶች ማምረቻ እና መሸጫ ተቋማት ላይ የንፅህና እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ሲሆን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው።

የደረጃ መነሻ ሰነዱን ያቀረበው የጤና ሚኒስቴር ነው።ኤጀንሲያችን ለሰነዱ አቅራቢ ምስጋናውን ያቀርባል ።

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

1. ወሰን

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ በሁሉም የዳቦ፣ ኬክ፣ ኩኪስና ደረቅ ጣፋጭ ብስኩቶች ማምረቻ እና መሸጫ ተቋማት ላይ የንፅህና እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ያካተተ መስፈርት ነው፡፡

2. ማጣቀሻ

3. ቃላትናትርጋሜ

3.1.

የዳቦ፣ ኬክ፣ ኩኪስና ደረቅ ጣፋጭ ብስኩቶች ማምረቻ እና መሸጫ

ዳቦ፣ ኬክና ደረቅ ጣፋጭ ብስኩቶችን ዱቄትን፣ ከስኳር፣ ከቅመማቅመም እና ከሌሎች ተጨማሪ ማጣፈጫ እና ማቅለሚያ ጋር በማዋሃድ፣ የቅርጽ እና ይዘት ለውጥ በማድረግ፣አምርቶ የሚሸጥ ተቋም ማለት ነው፡፡

3.2.

መፀዳጃ ቤት፡

ሰዎች በቁም ወይም በመቀመጥ ከሰውነት የሚወጣ ቆሻሻ(አይነ ምድር እና ሽንት) የሚያስወግዱበት መቀመጫ፣ በር፣ ወለል፣ ግድግዳ እና ጣሪያ/ኮርኒስ ያለው ክፍል ነው፡፡

3.3

የግልንፅህና

ሰው በራሱ ኃላፊነት በሽታ አምጪ ምቹ ሁኔታዎችን ለመከላከል እና ጤናን ለመጠበቅ የራስን እና የአልባሳት ንፅህና መጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራትን (ገላን መታጠብ እጅን በሳሙና መታጠብ አልባሳትን በንፅህና መያዝ) ማከናወን ማለት ነው፡፡

3.4

የማዘጋጃ/መጋገሪያ ክፍል፡

ዳቦና የመሳሰሉትን ምርቶች ለመስራት የሚያገለግሉትን ጥሬ ዕቃዎችን የማዋሃድ፣ የማቡካት፣ የመጋገር እና የማሸግ ሂደቶች የሚከናወንበት ዋናው ቦታ ማለት ነዉ፡፡

3.5

መጥፎ ሽታ

በሰው ልጅ ማሽተቻ አካል(አፍንጫ) ተስማሚነት የሌለው እና መጥፎ ስሜትን የሚፈጥር ማለት ነዉ፡፡

3.6

በቂ ብርሃን

ማንኛውም ማየት የሚችል ተጠቃሚ የሚገለገልበትን ክፍል አራቱን ምጥጎች ያለምንም ችግር ማየት የሚችልበት አካባቢ ማለት ነዉ፡፡

3.7

ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ

ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ፣ በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተሰራ፤ በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ ለማጽዳት ቅርፁ አመቺ የሆነ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል የቆሻሻ መሰብሰቢ ያማለት ነው፡፡

3.8

የውሃ አቅርቦት

ከከተማው የውሃ መስመር ወይንም አግባብ ባለው አካል ተመርምሮ ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲውል የተረጋገጠ የጉድጓድ ወይም ከሌሎች የውሃ መገኛ ምንጮች የተገኘ ውሃ ማለት ነው፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

3.9

የተሟላ እጅ መታጠቢያ

ሙቅና ቀዝቃዛ የቧንቧ ውሃ፣ፍሳሽ መቀበያ ከሴራሚክ (በብሎኬት/ግንብ) የተሰራገንዳ ፣ፈሳሽሳሙና ፣በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ማጽጃና የዕጅ ማድረቂያ ሶፍትና የፍሳሽ መስመር የተዘረጋለት ማለት ነው፡፡

3.10

የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሶች

በስራ ቦታ ለሚከሰቱ ማንኛውም በንክኪ የጤና ችግር ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች ለመከላከል ሲባል የሚለበሱ/የሚደረጉ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

4. አጠቃላይመስፈርቶች

4.1 የድርጅቱ አካባቢያዊ ሁኔታ ከነብሳት መራብያ ከቆሻሻ መጣያ መጥፎ ሽታ ከኬሚካል ወይም መርዝ ከሚከማችበትና በአጠቃላይ ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉና በሰው ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ መሆን የለበትም፡፡

4.2 በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙት ልዩልዩ የስራ ክፍሎች ወለል የተሰራበት ቁሳቁስ ሴራሚክስ/ታይልስ/ ሊሾ የሆነ ኮንክሪት ሆኖ አካላዊ ይዘቱም ያልተቦረቦረ ያልተሰነጠቀና በቀላሉ ሊጸዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

4.3 ሰራተኞች በሥራ ላይ የሚጠቀሙበት ከስስ ነጭ ጨርቅ የተዘጋጁ ሱሪ ኮት/ገዋን የፀጉር መሸፈኛ ቆብ ልብሶችና የትኩስ ነገር ማውጫ ወፍራም ጓንት ከእሣት አደጋ መከላከል የሚችል የደህንነት ጫማ እንዲሁም የአፍና የአፍንጫ፣ መሸፈኛ ማስክ ተሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4.4 ማንኛውም ሰራተኛ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ገላውን መታጠብ አለበት፣ንፅህናው የተጠበቀ የስራ ልብስ በስራ ላይ ለብሶ መገኘት አለበት፡፡

4.5 ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከምንጬ (በስራ ዕንቅስቃሴ ከሚመነጭበት ቦታ)መሰብሰብ አለበት፡፡

4.6 እንደ ድርጅቱ ስፋትና በውስጡ እንደሚገኙት ሰራተኞች ብዛት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መርጃ መስጫ ሳጥን ሊኖር ይገባል፡፡

4.7 በምግብ ማቀነባበሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ቦታ ላይ የተቀመጠ/የተሰቀለ የእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘር መዘጋጀት ወይም መኖር አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

5. ዝርዝርመስፈርቶች

5.1. የድርጅቱ አካባቢያዊ እና የህንፃ ዲዛይን ሁኔታ

ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎትም ሆነ የሚያመርተው ምርት ጋር ሊጣጣም የማይችልና በአገልግሎቱ ወይም በምርቱ ላይ የመበከል አደጋ ሊያስከትል ከሚችል ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ወይም አምራች ድርጅት ቢያንስ 50 ሜትር ርቀት ላይ መሆን አለበት፡፡

5.2. የውሃአቅርቦት

ከማጠራቀሚያ ጋኖች ለአገልግሎት የሚውለው ውሃ ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል ባለሙያ ናሙና ተወስዶ መመርመር አለበት፡፡ይህንንም የሚገልጽ መረጃ በድርጅቱ ለአንድ አመት ተደራጅቶ መቀመጥ አለበት፡፡

5.3. የጥሬ እና የተዘጋጁ ምርቶች ማከማቻ/መጋዘን

5.3.1. ማንኛውም የዳቦ መጋገሪያ ድርጅት ለሚሰጠው አገልግሎት ወይም ምርት የሚጠቀምባቸውን የጥሬ እቃዎች ለዚሁ ተብሎ ተለይቶ የተዘጋጀ፡ ኮርኒስ ያለው፣ ስፋቱ ቢያንስ 3ሜ በ3ሜትር፣ ቁመቱ ከ 2.5 ሜትር ያላነሰ የጥሬ እቃ ማስቀመጫ ክፍል ያለው መሆን አለበት፡፡

5.3.2. የደረቅ እቃዎች ማከማቻ የቅዝቃዜ መጠኑ ከ10ዲግሪ ሴልሽየስ እስከ 21 ዲግሪ ሴልሽየስ የሆነ የቅዝቃዜ ክፍል፡የቅዝቃዜ መጠኑ ከ2 እስከ 8 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሆነ የበረዶ ክፍል፡ የቅዝቃዜ መጠኑ ከ -18 ዲግሪ ሴልሽየስ እና ከዚያ በታች የሆነ መሆን አለበት፡፡

5.3.3. መደርደሪያው ወይም ፓሌቱ ከወለል 40 ሴ.ሜ፣ ከግድግዳ 20ሴ.ሜ፣ ከጣሪያ 60ሴ.ሜ ርቀት ያላቸውና በመደርደሪያዎች መሃል ቢያንስ አንድ ሰው በበቂ ሁኔታ ማንቀሳቀስ የሚችል (1 ሜትር) መሆን አለበት፡፡

5.3.4. ለዳቦ መጋገሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችና የሚበላሹ ተጨማሪ ነገሮች አንድ ጊዜ ከተከፈቱ በኋላ ከ3 ቀን በላይ አገልግሎት ላይ መዋል የለባቸውም፡፡

5.3.5. የቅዝቃዜ ክፍል፡ የቅዝቃዜ መጠኑ ከ2 እስከ 8 ዲግሪ ሴንቲግሬድ መሆን አለበት፡፡

5.3.6. የበረዶ ክፍል፡ የቅዝቃዜ መጠኑ ከ -18 ዲግሪ እና ከዚያ በታች መሆን አለበት፡፡

5.4. የማዘጋጃ/መጋገሪያ ክፍል

ስፋቱ ቢያንስ 30 ካሬ ሜትር ሆኖ የአንዱ ጐን መጠን ከ 3 ሜትር ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

5.5. መዳመጫ፣ ቅርፅ ማውጫናመ ቁረጫ

5.5.1. ለማዳመጫነት የሚያገለግል ጠረጴዛ አንድ ወጥ ከሆነ ዕምነበረድ ወይም ለምግብ ዝግጅት ደረጃ በተዘጋጀ ስቴይንለስስቲል የተሠራ ሆኖ ቢያንስ ከ 2 ካሬ ሜትር በላይ ሆኖ የአንድ ጐን ርዝመት ቢያንስ 1ሜትር መሆን አለበት፡፡

©ESA

5.5.2. የመጸመጫ ጠረጴዛ ከግርግዳ ያልተደገፈና 25 ሳ.ሜ የራቀ ሆኖ ከመሬት ቢ.ያንስ 1.20 ሜትር ከፍ ያለ መሆን አለበት፡፡

5.6 የእንጨት ማገዶ/እሳት መጋገሪያ

5.6.1 የእሳት ማጥፊያው በተገቢው ጊዜ እየተመዘገበ የሚ.ታደስ /የሚሞላ መሆን አለበት፡፡

5.6.2 ለማገዶነት ማቀጣጠያነት የሚ.ያገለግሉ እንጨትና የመሣሠሉት ነገሮች ከመ.ጋገሪ.ያ ክፍል ውጪ. ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ/ክፍል አግባቡን በጠበቀ ሁኔታ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

5.7 የዳቦ ማብረጃ/ማቀዝቀዣ መደርደሪያና ማጓጓዥ

5.7.1 በማቀዝቀዣ ላይ ያለ ዳቦ ለቆሻሻ በራሪና ቆርጣሚ ነፍሳት እንዳይ.ጋለጥ ንፅህናው በተጠበቀ ስስ ጨርቅ/ወረቀት መሸፈን ይኖርበታል፡፡

5.7.2 ዳቦን ከተመረተበት ቦታ ለማጓጓዝ የሚ.ያገለግል ዕቃ ከኘላስቲክ የተሠራ ሳጥን ሆኖ ክዳን/መሸፈኛ ያለውና በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

5.8 የእንጨት መጋገሪሪያ

5.8.1 አሠራሩ እሣትን እንዲቋቋም ከሸክላ ጡብ ሆኖ የጭስ ማውጫው ከፍታ ከጣሪያው በላይ ቢ.ያንስ 3 ሜትርና ከዚ.ያ በላይ ሆኖ አጐራባችን የማይረብሽ የማይበክል ሆኖ መሠራት ይኖርበታል፡፡

5.8.2 የመጋገሪያ ማስገቢ.ያው ከመሬት ቢ.ያንስ 1 አንድ ሜትር ከፍ ብሎ ከግርግዳ ደግሞ ቢ.ያንስ 30 ሳ.ሜ ራቅ ብሎ በሚ.ጋግረው ሰው ላይ ጉዳት በማያደርስ/በማያስከትል መሠራት ይኖርበታል፡፡

5.8.3 የእሣት ማጥፊያ ለድርጅቱ በመደበኛነት የሚጠየቀው እንዳለ ሆኖ ከዳቦ መጋገሪያው ቢ.ያንስ በ2ሜትር ርቀት የሚገኝና መጠኑም ቢ.ያንስ 5 ኪ.ግ እና ከዚ.ያ በላይና ዓይነቱም የካርቦንዳይኦክሳይድ እሣት ማጥፊያ መሆን አለበት፡፡

5.9 የኤሌክትሪክመጋገሪ

5.9.1 የመጋገሪያ ማሽኑ አቀማመጥ ከግርግዳ 30 ሳ.ሜ ርቀት ጠብቆ፣አመቺ በሆነ ቦታ ላይ የተቀመጠ ሆኖ የኤሌክትሪክ መሠኪ.ያዎችና መስመሮች አደጋ በማያስከትል ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

5.9.2 ዳቦ ከተጋገረ በኃላ ዳቦውን ለማቀዝቀዝ የሚ.ያገለግል መደርደሪያ የሚሰራበት ቁሳቁስ ከወንፊት ሽቦ፣ ከንፅህ ጣውላ ስስ እንጨት የተዘጋጀ ሆኖ ቢ.ያንስ ከመሬት 40 ሳ.ሜ ከፍታ ከግድግዳ 30 ሳ.ሜ እና ከኮርኒስ 40 ሳ.ሜ ዝቅ ብሎ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

5.10 የማሸጊያ ቦታ

5.10.1 ለማሸጊያ ስራ የምንገለገልበት ጠረጴዛ አንድ ወጥ ከሆነ ዕምነበረድ ወይም ለምግብ ደረጃ ይዘት በተዘጋጀ ስቴይንለስስቲል የተሠራ ሆኖ ቢ.ያንስ ከ 2 ካሬሜትር በላይ መሆን አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

5.11 መጸዳጃቤት

5.11.1 የክፍሉ ጣሪያ ከፍታ ቢያንስ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) መሆን አለበት

5.11.2 የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 1.2 ሜትር በ1.2 ሜትር (አንድ ነጥብ ሁለት ሜትር በአንድ ነጥብ ሁለት ሜትር) መሆን አለበት፡፡

5.11.3 ለ20 ሰራተኞች አንድ የመፀዳጃ መቀመጫ/ቀዳዳ ለወንድና ለሴት ለየብቻ የተለየ መኖር አለበት፡፡

5.12 የገላመታጠቢያ (ሻወር)

5.12.1 የክፍሉ ጣሪያ ከፍታ ቢያንስ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) መሆን አለበት፡፡

5.12.2 የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 1.5ሜትር በ1.5ሜትር (አንድ ነጥብ አምስት ሜትር በአንድ ነጥብ አምስት ሜትር) መሆን አለበት፡፡

5.12.3 የመታጠቢያ ክፍሉ ንጹህ አየር ማስገቢያ ከኮርኒስ 20ሳ.ሜ ዝቅ ብሎ በ45ዲግሪ ወደ ታች ተከፋች የሆነ መስኮት መኖር አለበት፡፡

5.12.4 ለ20 (ሃያ) ሰራተኛ/ተገልጋይ አንድ ሻወር ለወንድና ለሴት በሚል ንፅፅር የተለየ ሊኖር ይገባል፡፡

5.13 የሰራተኞች ጤና ምርመራ

5.13.1 ማንኛውም ከምግብ ጋር ንክኪ ያላው ሰራተኛ በየሶስት ወራት የሚደረግ የምግብ ወለድ ተላላፊ በሽታዎችን (በምግብ ሰራተኞች አማካኝነት ተላላፊ የሆኑ የምግብ ወለድ በሽታዎች) የጤና ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡

5.14 የእሳት አደጋ መከላከያ

5.14.1 እንደ ድርጅቱ አገልግሎትና ስፋት ክብደታቸው ከ2ኪ.ግ. ያላነሰ በካርቦንዳይኦክሳይድ የተሞሉ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች መኖር አለበት፡፡

5.15 የሰራተኞች ልብስ መቀየሪያ፣ ማረፊያና መመገቢያ ክፍል

5.15.1 የማምረቻ ድርጅቱ ለሰራተኞቹ ያዘጋጀውን የስራ ልብስ መቀየሪያ ክፍል ለወንድና ለሴት የተለያዩ ክፍሎች ሆኖ ስፋቱ እንደሰራተኛው ብዛት የሚወሰን ሆኖ ቢያንስ ለአነስተኛ ድርጅቶች 2በ2 ሜትር የሆነ ክፍል መዘጋጀት አለበት፡፡ ለምሳሌ ከ6 ዌም 8 ሰራተኞች በላይ ያላቸው ከሆኑ በሰራተኞች ልብስ መቀየሪያ ክፍል ውስጥ የሚቆለፉ 40ሳ.ሜ በ40ሳ.ሜ ስፋት ያላቸው ኮመዲኖዎች/ኪሶች ያሉት ቁም ሳጥን/ማስቀመጫ መዘጋጀት አለበት፡፡

5.15.2 የምግብ ማምረቻ ድርጅት ለሰራተኞቹ በምሽትና የአዳር የስራ ፈረቃዎች የሚተኙበት የማረፊያ ክፍል ለወንድና ለሴት የተለያዩ ክፍሎች ሆኖ ስፋቱ እነደሰራተኛው ብዛት የሚወሰን ሆኖ ቢያንስ 3ሜ በ3ሜ የሆነ ክፍል መዘጋጀት አለበት፡፡

5.15.3 በሰራተኞች ማረፊያ ክፍል ውስጥ 1 ካሬ ሜትር ስፋት እና 1.90 ሜትር ርዝመት ያላቸው አልጋዎች (ተደራራቢ ሊሆንይችላል) ድርጅቱ በምሽትና የአዳር የስራ ፈረቃዎች በሚያሰራቸው የሰራተኞች ብዛት ልክ መዘጋጀት አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

6. የድርጅቱ አካባቢያዊ እና የህንፃ ዲዛይን ሁኔታ

6.1. የድርጅቱ ክፍል ስፋት እንደሚሰጠው አገልግሎት ወይም እንደሚያመርተው ምርት ሆኖ በአገልግሎቱም ላይ ሆነ በምርት ላይ የመበከል፣የመመረዝ እና የመደበላለቅ ሁኔታ የማያመጣ ሆኖ ስራውን በትክክል ሊያሰራ በሚያስችል መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

7. የህንፃው ዲዛይን ሁኔታ

7.1. የድርጅቱ ህንፃውም ሆነ በውስጡ ያሉት ክፍሎች፣ መስኮትና በሮች የመሠረቱ አሠራር ውሃን፣ ተባይ፣ ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳትን የማያስገባ ሆኖ የድርጅቱ ህንጻ ያረፈበት ቦታ አፈር ዝናብም ሆነ ጎርፍ በቀላሉ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

7.2. ለአካል ውስንነት ላለባቸው የጋሪ መንቀሳቀሻ ምቹ የሆነ መወጣጫ (ራምፕ) መኖር አለበት፡ ፡

7.3. ህንፃው የተገነባበት የግንባታ ግብአት ከድንጋይ ከብሎኬት ከሸክላ ወይም ከተመሳሳይ ግብአት የተገነባ ሆኖ በሴሚንቶ ሊሾ የተለሰነና ልሙጥ/ለስላሳ ሆኖ የእሳት አደጋን መቋቋም የሚችል መሆን አለበት፡፡

7.4. ግድግዳበ ድርጅቱ ውስጥ የሚገኙት ልዩልዩ የስራ ክፍሎች ግርግዳ የተሰራበት ቁሳቁስ ሴራሚክስ/ታይልስ/ሊሾየሆነ/ የተለሰነ ብሎኬት /ድንጋይ/ ሸክላ ጡብ/ ሃይድሮፎም ሆኖ አካላዊ ይዘቱም ያልተቦረቦረ፣ያልተሰነጠቀ ክፍተት የሌለውና ነጭ/ ወይም ፈካ ያለ ቀለም የተቀባና በቀላሉ ሊጸዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

7.5. ኮርኒስ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙት ልዩልዩ የስራ ክፍሎች ኮርኒስ ያለው የተሰራበት ቁሳቁስ ከፐላስቲክ /ሲንቴቲክ ቲምበር/ ከጣውላ እንጨት /ፋይዚት/ ቺፑድ/ የተመረቱ ተገጣጣሚ ቦርዶች ሆኖ አካላዊ ይዘቱም ክፍተት የሌላውና ነጭ /ወይም ፈካ ያለ ቀለም የተቀባና በቀላሉ ሊጸዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

8. የአየር ዝውውርና የብርሃን ሁኔታ

8.1. በድርጅቱ ክፍሎች በቂ የአየር ዝውውር መኖር አለበት፡፡

8.2. አገልግሎት ለመስጠት በቂ የሆነ ብርሃን መኖር አለበት፡፡

8.3. አማራጭ የሃይል ምንጭ (generator) ሊኖር ይገባል፡፡

8.4. በክፍሉ ውስጥ ሊኖር የሚገባ የብርሃን መጠን 200ላክስ /ለእስቶር 50ላክስ /እና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ላይ 20 ላክስ መሆን አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

9. የውሃ አቅርቦት

9.1. በድርጅቱ የሚዘረጉ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች ሙሉ በሙሉ አላስፈላጊ ፍሳሽ ወይም ስርገት የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡

9.2. የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ከፕላስቲክ ወይም ከፋይበርግላስ(fiber glass) የተመረተ ሆኖ ውሃ በሚቋረጥበት ወቅት የመያዝ አቅሙ ቢያንስ ለሁለት ቀናትና ከዛ በላይ ማገልገል የሚችል መሆን አለበት፡፡

9.3. የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያ ጋን በየሶስት ወር መጸዳት እና በውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች መታከም አለበት፡፡

9.4. የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያ ጋን የጽዳት ሂደት የሚገልጽ መረጃ ተዘጋጅቶ ቢያንስ ለአንድ አመት ተደራጅቶ መገኘት አለበት፡፡

9.5. ለምርመራ የሚወሰደው የውሃ ናሙና ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የመጠቀሚያ ቦታዎች መሆን አለበት፡- ወደ ድርጅቱ ከሚገባ መስመር፣ ከማጠራቀሚያ ጋን፣ የዕቃ ማጠቢያ ቧንቧ፣ ከመታጠቢያ ቤት፣ ከዕጅ ማጠቢያ፣ ከመኝታ ክፍሎች፣ ከምግብ ማብሰያ ክፍሎች፡፡

10. የጥሬ እና የተዘጋጁ ምርቶች ማከማቻ/መጋዘን

10.1 . ድርጅቱ ለሚሰጠው አገልግሎት ጊዜያዊ ማከማቻ የሚሆን አግባብነት ያለው ክፍል እንዳስፈላጊነቱ ሊኖረው ይገባል (ወለል፣ግድግዳ፣ ኮርኒስ ያለው፤ ስፋቱ ቢያንስ 6 ካሬ ሜትር (2ሜX3ሜ ካሬ) የሆነ፤ የክፍሉ ኮርኒስ ከፍታ ከወለሉ ቢያንስ ከ2.4 ሜትር እና ከዚያ በላይ የሆነ)

10.2 . በውስጡ ከማይዝጉ እና በቀላሉ ሊፀዱ ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተሰራ መደርደሪያ መኖር አለበት፤ አቀማመጡም ከወለል 40 ሴ.ሜ.፣ ከግድግዳ፣ 20 ሴ.ሜ.፣ ከጣሪያ 60 ሴ.ሜ እና በመደርደሪያዎች መካከል አንድ ሜትር ባለው ርቀት መሆን አለበት

10.3 . የእቃ ማከማቻ ክፍል እንደ የሚቀመጥበት ጥሬ እቃ ወይም የተዘጋጁ ምርቶች አይነት የሙቀት መጠኑ የተለያየ መሆን አለበት፡፡

10.4 በክፍሉ ውስጥ የሚቀመጡ ማንኛውም ጥሬ እቃም ሆነ ምርት እንደ አገባበቸው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው (ቀድሞ የገባ ቀድሞ መውጣት አለበት)፡፡

10.5 . የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ጥሬ ዕቃዎችና እና ምርቶች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረው እና ከሌሎች ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች ተለይተው እና ተመዝግበው መቀመጥ አለባቸው፡፡

10.6 . ማንኛውም የዳቦ መጋገሪያ ድርጅት ከሌላ ድርጅት /መኖሪያ ቤት በአንድ ላይ ያልሆነና የራሱ የሆነ ህንጻ/ ቅጥር ግቢ ያለው ሆኖ በውስጡ ከዳቦ ማምረት ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች ስራዎች የማይከናወኑበትና አከባቢው ከማንኛውም ዓይነት አካለዊ፣ ኬሚካላዊ እና ስነ-ህይወታዊ ብክለትና ቆሻሻዎች የጸዳ መሆን አለበት፡፡

©ESA

10.7 . ማንኛውም ድርጅት የጥሬ ዕቃ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ጥሬ እቃዎች ለማስቀመጥ የሚጠቀምባቸው እቃ መደርደሪያ ወይም ፓሌት መኖር አለበት፡፡

10.8 . ለምግብ ማዘጋጃ የሚውሉ እና የንፀህና፣ ፅዳትና ሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

10.9 . ለዳቦና የመሳሰሉትን ለማዘጋጀት የሚውሉ የተለያዩ ዓይነት ጥሬ ዕቃዎች የገቡበት ቀን፣ ከየት እንደ መጡና የመገልገያ ማብቂያ ካላቸው ይኸው ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መዝገብና መከታተያ ካርድ መመዝገብና መያዝ ይኖርበታል፡፡

10.10 የማቡኪያ ማሽን ለምግብ ዝግጅት ደረጃ በተዘጋጀ ስቴንለስስቲል የተሠራ መሆን አለበት፡፡

10.11 ማቡኪያ ማሽን የሚወጣው ድምፅ /ንዝረት በሀንፃውና በዙሪያው ባሉ አጎራባቾች ላይ የድምፅ ብክለት የማያስከትል መሆን አለበት፡፡

10.12 በክፍሉ ውስጥ ቅዝቃዜ ለሚፈልጉ የኬክ እና የዳቦ ምርቶች ማስቀመጫ ማቀዝቀዣ ሊኖር ይገባል፡፡

10.13 ቅዝቃዜ ለሚፈልጉ የኬክ እና የዳቦ ምርቶች የተዘጋጁ ፍሪጆች በሙሉ የቅዝቃዜ መጠናቸውን የሚገልጽ ዲጅታል የሆነ የውጭ እና የውስጥ የቅዝቃዜ መለኪያ መሳሪያ (thermometer) ሊኖራቸው ይገባል፡፡

11. መዳመጫ፣ቅርፅ ማውጫና መቁረጫ

11.1 የተዳመጠን ሊጥን ለመቁረጥ፣ለመመዘንና ቅርፅ ለማውጣት የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ለምግብ ዝግጅት ደረጃ ከተዘጋጀ የስቴይንለስስቲል ቁሳቁስ የተሠራ መሆን አለበት፡፡

12. ማኮፈሻ

12.1 ሊጥን ለማኮፈስ የሚያገለግል ክፍል /ቦታ/ ማሽን ከማይዝግና ከማይቦሩቦር ስቴይንለስስቲል የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

12.2 የማኮፈሻ ክፍል ወይም ቦታ የተለያዩ ነፍሳቶችና ቆሻሻን በማያስገባ መልኩ የተዘጋጀ ሆኖ በትክክል የሚገጥሙ በሮች ሊኖረው ይገባል፡፡

12.3 ዳቦን ለማኮፈስ ወይም ለመጋገር የሚያገለግሉ ባትራዎች /ትሪዎች ለምግብ ደረጃ /ይዘት በተዘጋጀ ስቴይንለስስቲል የተሠሩና ንፅህናቸው የተጠበቀ መሆን አለባቸው፡፡

13. የማሸጊያ ቦታ

13.1. የማሸጊያ ዕቃዎች ምግቡን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን፣ክፍተት በሌለውና ለምግብ ማሸጊያነት ደረጃ ባላቸው ማሸጊያዎች /ፕላስቲክ/ ወረቀት/ አሊሙኒየም ፎይል መሆን ይኖርበታል፡፡ የእቃዎቹ ጥራት የኢትዮጵያ ደረጃን መስፈርት ማሟላት አለባቸዉ፡፡

13.2. በየምግብ ማሸጊያው ዕቃዎች ላይ የተመረተበት ቀን፣ የመጠቀሚያ /ማለቂያ ጊዜ፣የተሰሩበት ጥሬ ዕቃ ይዘትና መጠን፣ የምግብ ይዘት፣ፍቃድ ከተሠጣቸው ላቦራቶሪዎች በመረጃ በመጠቀስ/በማቅረብ ከተመረተበት ቦታ ሙሉ አድራሻ ጋር የተሟሉ መረጃዎች በማሸጊያው ላይ መኖር አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

13.3. በአንድ ተመሳሳይ የምርት ጊዜ የተመረቱ ምርቶችን ለመለየት በሚያስችል ተከታታይ የምርት መለያ ቁጥሮችን /ኮዶችን በቀላሉ በማይለቅ ህትመት/ቀለም ተጽፎ (ዕለትና መለያ ኮድ /የባች ቁጥር/ ሎት ቁጥር በማሸጊያው ላይ መኖር አለበት፡፡

14. ማጓጓዣ/ትራንስፖርት

14.1. ምርቱን የሚጓጓዘው በመኪና ከሆነ በህዝብ ትራንስፖርት ማጓጓዝ የማይቻል ሲሆን ከፀሃይ አቧራና ሌሎች ባዕድ ነገሮች በማያገኙት መልኩ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ተሽከርካሪ መጓጓዝ ይኖርበታል፡፡

14.2. ምርቶች ተጓጉዘው የሚደርሱበት ማከፋፈያ /መሸጫ አገልግሎት መስጫ ወይም ግለሰብ ከምርቱ መላያ ኮድና የተረከበበት ቀን ጋር ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ መረጃው ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

14.3. ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ ማጓጓዣ ሊኖር ይገባል፡፡

14.4. ለማጓጓዝ የሚያገለግል ማጓጓዣ ንፁህ፣ ደረቅና ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉ ከፀሐይ፣ከአቧራና ከማናቸውም እርጥበት ወይም ሌሎች ነገሮች የሚከላከል መሆን አለበት፡፡

14.5. ከዳቦና ኬክ ምርቶች ጋር የሚቃረን ባህሪ ያለው ወይም ሊበክል የሚችል ማንኛውም ዓይነት እቃ በተጫነበት ወይም በተቀመጠበት የመጓጓዣ እቃ ምግብን መጫን ወይም ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

14.6. ቅዝቃዜ ለሚያስፈልጋቸው የኬክና የዳቦ ምርቶች የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸውን መጠበቅ የሚያስችል ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ማጓጓዣ መኖር አለበት፡፡

14.7. የኬክና ዳቦ ምርቶች ጋር ንክኪ ያላቸው ማንኛውም የመያዣ እቃዎች በምግቡ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊያስከትል ወይም ሊበክል ከማይችል ቁሳቁስ የተሰሩ፣ ለአያያዝ አመቺ የሆኑ እና ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆን አለባቸው፡፡

15. ከምግብ ጋር ንክኪ ያላቸው ነገሮች የማፅጃ ኬሚካሎች

15.1. በምግብ ማቀነባበሪያ ክፍል ውስጥ የሚጠቀምባቸውን ከምግብ ጋር ንክኪ ያለቸው መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች፣ማሽኖችና የመሳሰሉትን ከቆሻሻ ሙሉ በሙሉ ለማጽዳት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ የምግብ ቁሳቁሶች ማጠቢያ ዲተርጀንት መኖር አለበት፡፡

15.2. በምግብ ማቀነባበሪያ ክፍል ውስጥ የሚጠቀምባቸውን ከምግብ ጋር ንክኪ ያለቸው መሳሪያዎች፣ቁሳቁሶች፣ማሽኖችና የመሳሰሉትን ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን ነጻ ለማድረግ የሚያስችል ጸረ-ተህዋስያን ማጽጃ (ዲስኢንፌክታንት) መኖር አለበት፡፡

15.3. የዳቦ መጋገሪያ ባትራዎችና ሊሎች የምግብ ዝግጅት ቁሳቁሶችን ለማለስለስ የሚጠቀሙበት ዘይት ንጹህ የምግብ ዘይት መሆን አለበት።

©ESA

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

16. መጸዳጃ ቤት

16.1. የክፍሉ ወለል እና ግድግዳ መታጠብ፣ መፅዳት የሚችል፣ በውሃ የማይቦረቦር እና ልስላሴ ካለው የግንባታ ቁሳቁስ መሰራት አለበት፡፡

16.2. መፀዳጃ ቤቱ በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቢያንስ በ10 ሜትር ርቀት የተሰራ መሆን አለበት፡፡

16.3. ክፍሉ ንፅህናው የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

16.4. ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ በመጸዳጃ ክፍል ውስጥ፡ - ወለል፣ ግርግዳና መቀመጫም ሆነ በዙሪያው የማይገኝ መሆን አለበት፡፡

16.5. ከመጥፎ ሽታ ነፃ መሆን አለበት፡፡

16.6. የክፍሉ በር በቀላሉ ከውስጥ በኩል መከፈትና መዘጋት የሚችል መሆን አለበት፡፡

16.7. በመጸዳጃ ቤቱ ዉስጥ በውሃ ግፊት የሚሰራ ፍሳሽ እና ጽዳጅ ማስረጊያ መኖር አለበት፡፡

16.8. ክፍሉ በቂ የሆነ ብርሃን ማግኘት አለበት፡፡

16.9. መጸዳጃ ቤት ውሰጥ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ (ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፃቸው አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችሉ) ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት፡፡

16.10. ከመፀዳጃ ቤቱ ቢበዛ በሶስት ሜትር ርቀት አገልግሎት የሚሰጥ አግባብነት ያለው በግድገዳ ላይ የተገጠመ ሲንክ/ገንዳ ከወራጅ ውሃ ጋር ያለው የእጅ መታጠቢያ ሊኖረው ይገባል፡፡

16.11. ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን ደረቅ ወይም ፈሳሽ ሳሙና መኖር አለበት፡፡

16.12. ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጊዜያት በሙሉ መፀዳጃ ቤቱ ለተገልጋይ ክፍት መሆን አለበት፡፡

16.13. የፍሳሽ መስመሩ ከመጸዳጃ ቤቱ ከወጣ በኋላ የመፈተሻ ባለ ክዳን ቀዳዳ (man-hole) መኖር አለበት፡፡

17. የገላመታጠቢያ (ሻወር)

17.1. የክፍሉ ወለል ወለል እና ግድግዳ መታጠብ፣ መፅዳት የሚችል፣ በውሃ የማይቦረቦር እና ልስላሴ ካለው የግንባታ ቁሳቁስ መሰራት አለበት፡፡

17.2. የክፍሉ ወለል በጽዳትና በአገልግሎት ወቅት ምንም አይነት ፍሳሾችን አቁሮ መያዝ የለበትም፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

17.3. ሻወር ቤቱ ከመፀዳጃ ክፍል የተለየ እና ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ መሆን አለበት

17.4. የክፍሉ በር በቀላሉ ከውስጥ በኩል መከፈትና መዘጋት የሚችል መሆን አለበት፡፡

17.5. ለመታጠቢያ ቦታ አደጋን የሚከላከል ከፕላስቲክ የተሰራ መረጋገጫ መዘጋጀት አለበት ፡፡

17.6. ሻወር ለወንድና ለሴት በሚል ንፅፅር የተለየ ሊኖር ይገባል፡፡

17.7. በቂ የሆነ የአየር ዝውውር ሊኖረው ይገባል፡፡

17.8. የፍሳሽ መስመሩ ከተፈቀደለት የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር ወይም ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን ጋር የተገናኘ መሆን አለበት፡፡(ሴፕቲክ ታንከር ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የተሰራ፣ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነ/ድፍን የሆነና ወደ ውጭም ሆነ ወደ ውስጥ ፍሳሽ በማያሰርግ የግንባታ ቁሳቁስ የተሰራ መሆን አለበት)፡፡

18. የሰራተኞች የግል ንፅህና አጠባበቅ

18.1 እጅንቀጥሎ ከቀረቡት ተግዳራትና ሁኔታዎች በየጊዜውበሳሙናመታጠብያስፈልጋል፤

- ከመጸዳጃ ቤት መልስ፤
- በስራ መሃል ዕረፍት ከተሰወሰደ በኋላ፤
- ማንኛውንም የሰውነትን አካል በስራ መሃል ከተነካ በኋላ፤
- ከምግብ በፊትና በኋላ፤
- ቆሻሻ ወይም ማንኛውም የማጽጃ ቁስና ኬሚካሎች ከተነካ በኋላ፤
- ማንኛውንም የጽዳት ስራ ከማከናወን በኋላ፤
- ጓንት ከመጠቀም በፊትና በኋላ፤
- የእጅ ጥፍርን በየጊዜው በአጭሩ መቆረጥ ያስፈልጋል፤
- የምግብ ዝግጅት ላይየ ተሰማሩ ሰራተኞች፡ ተንጠልጣይ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ ቀለበት፣ ሰአት እና የእጅ አንባር በስራ ቦታ መደረግ የለበትም፤
- ፀጉር ሙሉ በሙሉ ሊሸፍኑ በሚችሉ የስራ ኮፍያዎች መሸፈን አለበት፡፡

18.2 ማንኛውም ሰራተኛ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት የእጅ ጥፍርን በየጊዜው በአጭሩ መቆረጥ አለበት፡፡

18.3 ማንኛውም ሰራተኛ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ተንጠልጣይ የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ ቀለበት፣ሰአት እና የእጅ አምባር ጌጣጌጦች ከረባት፣ የተንዘላዘሉ የአንገት ጌጦች በስራ ላይ ማድረግ የለበትም፡፡

18.4 ማንኛውም ሰራተኛ በስራ ወቅት ፀጉሩን ሙሉ በሙሉ ሊሸፍኑ በሚችሉ የስራ ኮፍያዎች መሸፈን አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

19 የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ

19.1 ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰብሰቢያ ክዳን ያለውና በእግር ተረግጦ የሚከፈትና የሚዘጋ ጊዜያዊ እና በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማጠራቀሚያ/ማቆያ መኖር አለበት (ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፃቸው አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችሉ)

19.2 የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የሚቀመጡበት ቦታ አካባቢ ንጽህናው የተጠበቀ ከተባይ፣ከነፍሳት እና ከቆርጣሚ እንስሳት ነፃ መሆን አለበት፡፡

19.3 በተቋሙ የተለያዩ ቦታዎች የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች/መሰብሰቢያዎች መቀመጥ አለባቸው፡፡

19.4 ድርጅቱ የደረቅ ቆሻሻን በአይነት እና በባህሪያቸው (የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ) በመለየት መሰብሰብና ማስወገድ አለበት፡፡

19.5 ድርጅቱ የመጨረሻ/አጠቃላይ የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ ከድርጅቱ ለሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ ተመጣጣኝ የሆነ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት (ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፁ አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል እና እንደ ቆሻሻው አይነት የተለየ)፡፡

19.6 መጨረሻ የተሰበሰበው ቆሻሻ በተገቢው መንገድ መወገድ አለበት፡፡

20 የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

20.1 ድርጅቱ በአግባቡ የተሰራ በፕላን የተዘረጋ ፤ ከእይታ የተሸፈነ፣ ወደ ውጪ ፍሳሽ የሌለው የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

20.2 ድርጅቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች (ከዕቃ ማጠቢያና ከዕጅ መታጠቢያ ሲንክ፣ ከመታጠቢያ ክፍሎች፣ ከመጸዳጃ ቤትየሚመነጭ ማንኛውም ፍሳሽ ቆሻሻ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ በተሰራ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን (ሴፕቲክ ታንክ፡ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነወደ ውጭም ሆነ ወደ ውስጥ ፍሳሽ በማያሰርግ የግንባታ ቁሳቁስ የተሰራ) ወይም ከተፈቀደ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

20.3 ድርጅቱ የፍሳሽ ቆሻሻን ለመሰብሰብ የሚጠቀመው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋን (ሴፕቲክ ታንክ) ከሆነ ሊሞላ 50 ሳንቲ ሜትር ሲቀረው መመጠጥ አለበት፡፡

20.4 ማንኛውም የፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ዝናብ ውሃ ማስወገጃ መስመር ወይም ወደ አካባቢ መልቀቅ የለበትም፡፡

20.5 የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የሚመለከተው አካል ከተፈቀደ የፍሳሽ መስመር ጋር የተያያዘበት፤የተጠራቀመ ፍሳሽ የተመጠጠበት ሲጠይቅ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

21 የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች

21.1 ነጭ ሙሉ የስራ ልብስ (ሁለት ቅያሬ)፣ የፀጉር መሸፈኛ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ (እንደ ስራው ሁኔታ)፣ የደህንነት መጠበቂያ ጫማ፣ የእጅ ጓንት (ልዩ ልዩና ቅያሪ)፣ፕላስቲክ ሽርጥ መኖር አለበት፡፡

22 የሰራተኞች ጤና ምርመራ

22.1 ሰራተኛው ከድርጅቱ ስራ ሲለቅ /ሲያቋርጥ የጤና ምርመራ ካርዱን ይዞ መሄድ አለበት፡፡

23 የእሳትአደጋ መከላከያ

23.1 የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ግልጽ በሆነ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን መቀመጥ አለበት፡፡

23.2 የእሳት አደጋ መከላከያው ጊዜውን ጠብቆ መታደስ አለበት፡፡

23.3 በድርጅቱ የሚሰሩ ሰራተኞች ስለእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ አጠቃቀም ስልጠና ሊወስዱ ይገባል፡፡

24 የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መርጃ መስጫ ሳጥን

24.1 የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መርጃ መስጫ ሳጥን ግልጽ በሆነ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን መቀመጥ አለበት፡፡

24.2 የተሟላ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች መያዝ አለበት፡፡ (ጥጥ፣ አልኮል፣ ጎውዝ፣ ሳቭሎን፣ ጂቪ፣ መቀስ፣ ግላቭ/ጓንት፣ የቁስልፕላስተር፣ ባንዴጅ፣ ቅባት/ፀረ-ተህዋስያን)

24.3 በመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ሳጥን ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መሆን የለበትም።

25 የተባይ፣ የነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳት መከለከልና መቆጣጠር

25.1 በድርጅቱ ውስጥ ምንም አይነት ተባይ፣ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳት መኖር ወይም ስለመኖራቸው የሚያሳዩ ምልክቶች መኖር የለበትም፡፡

25.2 ድርጅቱ ተባይ ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳት እንዳይኖሩ እንዲሁም ሲገኙ የሚቆጣጠርበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

25.3 ድርጅቱ ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ የተባይ፣ነፍሳት እና የቆርጣሚ እንስሳት የመቆጣጠርና መከላከል ስራ በባለሙያ ታግዞ ማሰራትና ስለማሰራቱም አስፈላጊውን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

26 የሰራተኞች ልብስ መቀየሪያ፣ ማረፊያና መመገቢያ ክፍል

26.1 የምግብ ማምረቻ ድርጅት ለሰራተኞቹ ያዘጋጀውን የስራ ልብስ ማጠቢያ በግርግዳ ላይ ከተገጠመና ቧንቧ ካለው ገንዳና የልብስ ማጠቢያ ሳሙና ጋር ማዘጋጀት አለበት፡፡

28. ሲጋራን በተመለከተ

28.1 ድርጅቱ ሲጋራ ማጨስ የሚከለከልበትን አዋጅ መተግበር አለበት፡፡

29. የድምጽ ብክለትን በተመለከተ

29.1. ከድርጅቱ ማሽነሪዎች በስራ ሰዓት የሚወጣው የድምጽ መጠን ከ90 ዴሲ ብል በታችና በሌሊት ደግሞ ከ40 ዴሲብል ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

29.2. ማምረቻ ማሽነሪዎች ድምጽን ውጠው ማስቀረት በሚችሉ ቁሳቁሶች ሊከለሉ ይገባል፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ
Ethiopian Standards Agency

Organization and Objectives

The Ethiopian Standards Agency (ESA) is the national standards body of Ethiopia established in 2010 based on regulation No. 193/2010.ESA is established due to the restructuring of Quality and Standards Authority of Ethiopia (QSAE) which was established in 1998.

ESA's objectives are:-

- Develop Ethiopian standards and establish a system that enable to check whether goods and services are in compliance with the required standards,
- Facilitate the country's technology transfer through the use of standards,
- Develop national standards for local products and services so as to make them competitive in the international market.

Ethiopian Standards

The Ethiopian Standards are developed by national technical committees which are composed of different stakeholders consisting of educational Institutions, research institutes, government organizations, certification, inspection, and testing organizations, regulatory bodies, consumer association etc. The requirements and/ or recommendations contained in Ethiopian Standards are consensus based that reflects the interest of the TC representatives and also of comments received from the public and other sources. Ethiopian Standards are approved by the National Standardization Council and are kept under continuous review after publication and updated regularly to take account of latest scientific and technological changes. Orders for all Ethiopian Standards, International Standard and ASTM standards, including electronic versions, should be addressed to the Documentation and Publication Team at the Head office and Branch (Liaisons) offices. A catalogue of Ethiopian Standards is also available freely and can be accessed in from our website.

ESA has the copyright of all its publications. No part of these publications may be reproduced in any form without the prior permission in writing of ESA.

International Involvement

ESA, representing Ethiopia, is a member of the International Organization for Standardization (ISO), and Codex Alimentarius Commission (CODEX). It also maintains close working relations with the International Electro-technical Commission (IEC) and American Society for Testing and Materials (ASTM).It is a founding member of the African Regional Organization for standardization (ARSO).

More Information?
Contact us at the following address.
The Head Office of ESA is at Addis Ababa.

☎ 011- 646 06 85, 011- 646 05 65
011-646 08 80
✉ 2310 Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: info@ethiostandards.org,
Website: www.ethiostandards.org

Standard Mark

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD